

# የትንቢት ቃል

ወቅታዊ የአድቬንቲስት መጽሔት

ሰባተኛ ዓመት, ቁጥር 2

ታህሳስ 2005

## የመልካም ስጦታዎች አመት በዓል

በ ሔለን ጂ ኋይት

መላው አለም የገና በዓልን (Christmas) ያከብራል። ለትንሹም ሆነ ለትልቁ፣ለወጣትም ሆነ ለአዛውንት የገና ወቅት የደስታ ወቅት ነው። ለምንድን ነው ግን ለዚህ አመት በአል ልዩ አተኩሮ የሚሰጠው? ሰዎች ታህሳስ 25 የየሱስ ክርስቶስ የልደት ቀን ነው በማለት በሁሉም ቦታ እንደ ልዩ በአል ቀን ያከብሩታል። ይህ ቀን ግን በርግጥ ጌታ የተወለደበት ቀን ለመሆኑ ምንም ማረጋገጫ የለም። ትክክለኛውን ቀን ማወቅ ለደህንነታችን ጠቃሚና አስፈላጊ እንደሆነ ቢያስብ ኖሮ እግዚአብሔር ይህንን በነቢያት ወይም ደግሞ በሐዋሪያት አማካኝነት ያሳውቀን ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ጉዳይ ምንም አለመግለጹ የሚያሳየው ሊሰጠው የሚገባው ክብር ለቀኑ ሳይሆን የአለም አዳኝ ለሆነው ለክርስቶስ እንዲሆን እግዚአብሔር እንደጠቢብነቱ አስቀድሞ ስላሰበ ነው።

የገና በአል «የየሱስ ክርስቶስ የልደት ቀን ነው» ተብሎ በሕብረተሰቡ የሚከበር የብዙ አመታት ባህል፣ለልጆችም የሚተረክና ዝም ብሎ ሊታለፍ የማይቻል ወቅት ስለሆነ ይህ ቀን የደስታ ቀን ሊሆን ይገባል። እንዲያውም ይህ ቀን ለክርስቲያኖች በጎ ነገርን ለማድረግ ጥሩ አጋጣሚ ሊሆንላቸው ይችላል። የዚህን አመት በአል በልዩ መልኩ የማክበር ፍላጎት አይከልከል። ቢሆንም ትክክለኛውን መንገድ እንዲይዝ ይደረግ። ልጆች የሚመኙትን የስጦታዎች መለዋወጥ (መሰጣጠት) ምኞት መልካም መልክ እንዲይዝ ማድረግ ይቻላል። ለሌሎች ሰዎች



መልካም ነገርን በማድረግ የክርስቶስን የወንጌል ሥራ ማጠናከር እንችላለን።

የገና ወቅት ሲደርስ ወሬው ሁሉ ስለስጦታ ነው። ትንሹም ሆነ ትልቁ «ለወዳጄ ምን አይነት ስጦታ በመስጠት ለእርሱ ያለኝን ፍቅር ልግለጽለት?» ብሎ ያስባል። ከሚወዱን ሰዎች ትንሽ ነገርም ብትሆን ስጦታን ስናገኝ ደስ ይለናል። ይህ፥ ወዳጆቻችን እኛን እንዳልዘነጉንና ልብ ለልብ የበለጠ የተሳሰርን እንደሆንን ያሳየናል። የመጀመሪያውን ቦታ ከያዘው ወዳጃችን ከእግዚአብሔር እስካለስበለጥናቸው ድረስ እርስ በርሳችን አንዱ ለሌላው ያለውን ፍቅር የሚገልጽበት ምልክት (ስጦታ) መለዋወጥ አለብን። የምንሰጠውም ስጦታ ለወዳጆችን የሚጠቅመው መሆን አለበት። መጽሐፍ ቅዱስን የበለጠ የሚገልጹ ወይም ደግሞ ለእግዚአብሔር ትእዛዛት ያለን ፍቅር እንዲጨምር የሚረዱ መጽሐፍትን ብንሰጣጥ ነው እኔ የምመክረው። በተለይ በእነዚህ ረጅም የብርድ ወራቶች የሚነበቡ መጽሐፍቶችን እንሰጣጥ። ሕጻናቶችም እንዲሁ በመጽሐፍት ስጦታ ይደሰቱ። ለጣፋጭ ነገሮችና ለማይረቡ መጫወቻዎች የሚወጣው ብዙ ገንዘብ ጠቃሚ በሆኑ መጽሐፍት ላይ ቢውል ይሻላል።

### የሱስን አትርሱት

ወንድሞቼና እህቶቼ፥- እርስ በርሳችሁ ስጦታ ስትሰጣጡ በሰማይ ያለውን ወዳጃችሁን አትርሱ! እያንዳንዱ በሚችለው መጠን ለእግዚአብሔር ስጦታን ያቅርብ። አምላክን በልባችሁ አክብሩት፣ምስጋናውም ከአፋችሁ አይለይ። አለም ይህንን በዓል በቅንጦትና ተገቢ ከሆነው በላይ ያከብራል። ለታይታና

(በገጽ 4 ይቀጥላል)

## ለዚያኛው ቀን መዘጋጀት

ታሪኩ የሚያወሳው በደቡብ ባህር ደሴት (South Sea Island) መርከቡ የተሰበረችበትና ያገሬው ሰዎች በትከሻቸው ተሸክመው ወደ መንደራቸው ወስደው ስላነገሡት መርከበኛ ነው። ሰውየውም ቀስ በቀስ ሲመረምር፤ይህ እየወሰዱ አንድን ሰው ለአንድ አመት ማንገሥ ባህላቸው መሆኑን ይረዳል። ይህንን ባህላቸውን በጣም ቢወደውም «ከርሱ በፊት ነግሠው የነበሩት ነገሥታት ከምን ደረሱ?» የሚለው ጥያቄ ግን እረፍት ሊሰጠው አልቻለም። ከጥቂት ጊዜ በኋላም እያንዳንዱ ንጉሥ የአንድ አመት የንግሥና ጊዜውን ሲፈጽም ተይዞ ምድረበዳ ወደሆነችው ጎረቤት ደሴት በረሀብ እየተሰቃየ ለሞት እንዲዳረግ ወደዚያ እንደሚላክ ይደርስበታል። ይህ ሃሳባቸው ያሳሰበው መርከበኛ በጣም ብልህ ስለነበረ የንጉሥነት ሥልጣኑን ተጠቅሞ አናጺዎቹ ጀልባዎችን እንዲሠሩ፣ ገበሬዎቹንም ወደ ምድረበዳዋ ደሴት ዘር ወስደው እንዲዘሩና እንዲያለሟት ግንበኞቹን ደግሞ ቤቶችንና ሕንጻዎችን በደሴትዋ ላይ እንዲሠሩ አዘዛቸው።

(በገጽ 6 ይቀጥላል)

### በዚህ እትም ውስጥ

| | |
|---|---|
| የመልካም ስጦታዎች አመት በዓል | 1 |
| ለዚያኛው ቀን መዘጋጀት | 1 |
| ከአዘጋጆች | 2 |
| «ትወደኛለህን? ትወጂኛለሽን?» | 2 |
| ከአንባቢዎች | 2 |
| ቃለ መጠይቅ | 3 |
| የኤች.አይ.ቪ(ኤድስ) የምክር አገልግሎት | 4 |
| 144000 ዎቹ እነማን ናቸው? | 5 |
| የመከራ ዘመን (ክፍል1) | 6 |
| መንግሥተ ሰማያት ለብርቱዎች | 7 |
| የሃይማኖቱ አለም ወቅታዊ ዜናዎች | 7 |
| የጥያቄዎ መልስ | 8 |



## ከአዘጋጆች

***የተወደዱ አንባቢ ሆይ!***

እንደገና ደግሞ የገና ወቅት ደረሰ። የገና በዓል ለምእራቡ አለም የቤተሰብ በዓል ስለሆነ ለረጅም ጊዜ ያልተያዩ የቤተሰብ አባላት የሚገናኙበት፣አብረው የሚበሉበትና የሚጠጡበት፣የሚጫወቱበትና ስጦታ የሚሰጣጡበት ልዩ ጊዜ ነው። በአገራችን ደግሞ የገና በዓል ትልቅ ድግስ የሚዘጋጅበት፣ቤተሰብ፣ዘመድ አዝማድና ጓደኞች እርስ በርሳቸው እየተገባበዙ የሚደሰቱበትና የክት ልብሳቸውን ለብሰው በአደባባይ እየተዘዋወሩ አገሩን የሚያደምቁበት እለት ነው። በአገራችንም ሆነ በውጭ አገር ይህ በዓል ማህበራዊነት የሚተኮርበትና አንዱ ለሌላው ያለውን ፍቅር በልዩ መልኩ የሚገልጽበት ጊዜ ሆኖ ይከበራል። ውድ አንባቢ፥ እርስዎስ ይህንን የልደት ወቅት እንዴት፣ከማንስ ጋር ይሆን ለማሳለፍ ያቀዱት? ዘመድዎ ወይም ወዳጅዎ ቤት ተጋብዘዋልን? ወይስ እርስዎ ወደቤትዎ ሰውን ለመጋበዝ አስበዋል?

ስለዚህ የገና ወቅት በማሰብ ላይ ሳለን በወንጌል ሉቃስ ውስጥ የተጻፈው የጌታ ምክር ወደ ሃሳባችን መጣ «የምሳ ወይም የእራት ግብዣ በምታደርግበት ጊዜ በአጸፋው እንዳይጋብዙህና ብድራትን እንዳይመልሱልህ ወዳጆችህን ወይም ወንድሞችህን ወይም ዘመዶችህን ወይም ከበርቴ ጎረቤቶችህን አትጋብዝ፤ነገር ግን ግብዣ ባዘጋጀህ ጊዜ ድሆችን፣አካለ ስንኩሎችን፣ሽባዎችንና አይነ ስውሮችን ጥራ፤ትባረካለህም። እነዚህ ብድር ሊመልሱልህ ስለማይችሉ ብጹእ ትሆናለህ፤ በጻድቃንም ትንሳኤ ብድራትህ ይመለስልሃል» (ሉቃ14፥12-14)

ታዲያ እኛ እና እርስዎ ይህንን ምክር በተግባር ከማዋል ምን ያግደናል? በዚህ ቀን አብረነው የምናሳልፈው ሰው እጅግ በጣም እንደሚደሰትና ከልብ የመነጨ ምስጋና እንደሚያቀርብ ምንም ጥርጥር የለውም። ባልንጀራዬ ሲደሰት ከማየት የሚበልጥ በምድር ላይ ምን ሌላ የሚያረካ ነገር አለ?።

በዚህ መንፈስ መልካሙን የሚመኙላችሁ፥

***የናንተው***
***ዳዊት መሐሪ እና ዳዊት መንግሥቱ***

ወንጌል

# «ትወደኛለህን? ትወጂኛለሽን?»

በዮሐንስ ወንጌል ምእራፍ 21 ቁጥር 15-17 ላይ ጌታ የሱስ ስምኦን ጴጥሮስን «የዮና ልጅ ስምኦን ሆይ ትወደኛለህን?» ብሎ ሶስት ጊዜ ሲጠየቀው፤ስምኦን መልሶ «አዎ ጌታ ሆይ እንደወድህ አንተ ታውቃለህ» በማለት እርሱም ሶስት ጊዜ አረጋገጠለት። ከዚያም ጌታ ለጴጥሮስ፥ «ግልገሎቼን አሰማራ፣ጠቦቶቼን ጠብቅ፣በጎቼን አሰማራ» በማለት አደራን ሰጠው። ከእዚህ ንግግር ውስጥ ክርስቲያኖች ሶስት ዋና ዋና ነገሮችን እንማራለን፥-

1ኛ) ጌታ የሱስ እንዲያገለግሉት፣ቤቱን እንዲያስተዳድሩለት እና ምእመናንን እንዲጠብቁለት አደራ የሚላቸው ሰዎች እንደ ጴጥሮስ ያሉ ሰዎችን ነው። የሱስ አንድ ጊዜ ጴጥሮስ እንደሚክደው ያውቅ ነበር፣ቢሆንም «ስምኦን ሆይ ... እኔ እምነትህ እንዳይጠፋ ስለ አንተ አማለድሁ አንተም በተመለስህ ጊዜ ወንድሞችህን አጽና» በማለት አስቀድሞ ነገረው። የሱስ እንደ ጴጥሮስ ባሉ ደካሞች ይተማመናል፣ቤቱን መምራት እንደሚችሉም ሙሉ እምነት አለው። የእርሱ ኃይል በእነርሱ ደካማነት ውስጥ እንደሚገለጥም ያውቃል። ስለዚህ ጌታ የሱስ እንዲያገለግሉት የሚመርጣቸው ሰዎች ፍጹማን አይደሉም ፣ ቢሆንም ግን ልክ ጴጥሮስን እንኪሞት ድረስ እንደረዳው፤ በአገልግሎትና በመንፈሳዊ ሕይወት እንዲያድጉ ይረዳቸዋል ።

2ኛ) እውነተኛ አገልግሎት በፍቅር ላይ የተመሠረተ ነው። የሱስ ጴጥሮስን ሶስት ጊዜ «ትወደኛለህን?» ሲል ልብን የሚመረምር ጥያቄ ጠየቀው። ጴጥሮስም በጣም እንደሚወደው ካረጋገጠለት በኋላ ነበር የሱስ ከላይ የተጠቀሰውን አደራ የሰጠው። አገልግሎቱ ውጤታማ እንዲሆን ጴጥሮስ በፍቅር መመሥረት ነበረበት። ፍቅር የሌለው አገልግሎት የሚያሰለች እና ዘለቄታ የሌለው ሥራ ነው የሚሆነው። ስለዚህ የየሱስ አገልጋዮች የክርስቶስ ፍቅር ግድ ብሎአቸው እንዲያገለግሉት ያስፈልጋል። ጌታ የሱስ ወደዚች ኃጥያተኛ ምድር መጥቶ ለማገልገል የወሰነው ፍቅሩ ግድ ስላለው ነው። ስለዚህ የእርሱ አገልጋዮችም እንዲሁ ከዚህ አይነት ፍቅር ተነስተው እንዲያገለግሉት ይሻል።

3ኛ) መገልገል ያለባቸው እነማን እንደሆኑ ይነግረናል። «በጎቼን አሰማራ፤ግልገሎቼን ጠብቅ» ሲል እነማንን ማለቱ ነው? ኤለን ጂ ዋይት እንዲህ በማለት ጽፋለች፥ «ጴጥሮስ ሙሉ በሙሉ አዲስ ሰው እንደሆነ የሱስ አውቆ ነበር። ሕይወቱን አሳልፎ የሰጣቸውን ነፍሳት ሁሉ ለጴጥሮስ አደራ ሰጠው። ለጴጥሮስ የተሰጠው አደራ በጎቹን ብቻ ሳይሆን ግልገሎቹንም እንዲያሰማራ ነው። ጴጥሮስ ወንጌልን ላልሰሙት ወንጌልን መስበክ ብቻ ሳይሆን ፣ የመንጋው እረኛም መሆን ነበረበት። ይህም ብዙ ጥንቃቄ የሚጠይቅ ሥራ ነው»።

ለእኛም በምድር ታሪክ መጨረሻ ጊዜ ለምንኖር ክርስትያኖች ይህ አደራ ተሰጥቶናል። ዛሬም ጌታ ልባችንን የሚመረምር ጥያቄ ይጠይቀናል፥ «ትወደኛለህን?» ከወደድከኝ በጎቼን አሰማራ፣ግልገሎቼን ጠብቅ!። ይህ አደራ ደግሞ ለአገልጋዮች ብቻ ሳይሆን ለእያንዳንዱ ምእመን የተሰጠ ነው።

የአገልግሎትን በረከት ከቀመሰ በኋላ ሐዋሪያው ጴጥሮስ እንዲህ ሲል ጻፈ፥ «እናንተ ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁ ፣ የእርሱን በጎነት እንድትነግሩ የተመረጠ ትውልድ፣የንጉሥ ካህናት፣ቅዱስ ሕዝብ፣ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ...»1ጴጥ 2፣9-10

ወገኖቼ ሆይ! እንደብርሃን ልጆች ፣ እንደ ተመረጠ ትውልድ፣እንደንጉሥ ካህናት፣እንደቅዱስ ሕዝብ እና እንደተለየ ወገን ሆነን እንድንመላለስና የአምላካችንን በጎነት እንድንናገር በዚህ በሚጀምረው በፈረንጆች አዲስ አመትም ሆነ በሕይወት ዘመናችን ሁሉ እግዚአብሔር ጸጋውን ያብዛልን።◆

***ዳዊት መሐሪ***

## ከአንባቢዎች

ውድ የትንቢት ቃል አዘጋጆች! ጤንነታችሁና መንፈሳዊ ሕይወታችሁ እንዴት ነው? መጽሔታችሁን ስመለከት በጣም ተደነቅሁኝ። አገልግሎታችሁን በማድነቅ ብቻ መቆየት አልፈልግም የአገልግሎታችሁ ተካፋይ ብሆንም ደስ ይለኛል። እስከዛው ድረስ መጽሔታችሁን ዘወትር ላኩልኝ። የእግዚአብሔር ጸጋና በረከት ከእናንተ ጋር ይሁን

***በክርስቶስ ወንድማችሁ***
***ናትናኤል ሚሊዮን ከአዋሳ***

የተወደዳችሁ አዘጋጆች «አንድ ምእራፍ ቢጠይቅህ እጥፉን መንገድ አብረኸው ሂድ» ማቴ 5፥41 የተጠየቀውን ብቻ ሳይሆን ከጠየቀው በላይ የምታደርጉ ናችሁ። ጽሑፌን ማውጣት አነሰና እኔ ምንም ሳልጠይቃቸሁና ሳላለምናችሁ መጽሐፌን ከነፎቶግራፉ በኢንተርኔት አወጥታችሁ ለህዝብ ስላስተዋወቃችሁልኝ ከልብ አመሰግናለሁ። የዋላችሁልኝ ውለታ ትልቅ ነው። ማመስገን ብቻ ሳይሆን እኔም ቢሆን ሌሎችም አንባቢዎች እንደተቻለ በገንዘብ ቢረዱ እንዴት መልካም ነበር!። ሙሉ አርጋው የጻፈችውን ግጥም አነብቤዋለሁ፣ሙሉ በርቺ!። የፍሬ ሕይወት ኃይሉ ታሪክ ይነካል። አድራሻዋ ቢሰጠን ነጻነቷን እስክታገኝ ድረስ በጸሎት ብቻ ሳይሆን በደብዳቤም ልናስታውሳት ይገባል። ከፍ ካለ ምስጋና ጋራ።

***ወንድማችሁ ግርማ ዳምጤ ከአሜሪካ***

በወንድም ግርማ ዳምጤ አማካኝነት የዚህችን እትም ወጪ ለሸፈኑላን በአንግዊን (ካሊፎርኒያ) ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን አድቬንቲስት ወንድሞችና እህቶቻችን ከልብ የመነጨ ምስጋናችንን ልናቀርብ እንወዳለን። ለዚህ ከፍቅር የመነጨ ስጦታችሁ ጌታ አብዝቶ ይባርካችሁ! ***አዘጋጆች***

# ቃለ መጠይቅ ከአዲሱ የኢትዮጵያ ዩኒየን ፕሬዚደንት ጋር

***ፓስተር አለሙ ሃይሌ፥ ከትንቢት ቃል መጽሄት ጋር ቃለ መጠይቅ ለማድረግ ፈቃደኛ ስለሆንክ በቅድሚያ እናመሰግናለን። በመጀመሪያ ራስህን በአጭሩ ብታስተዋውቀን?***

በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ዩንየን ውስጥ ጌታን በማገልገል ላይ ነው ያለሁት:: ለአለፉት 15 አመታት ጌታ በሰጠኝ ጤንነትን ኃይል አገሬን ቤተክርስቲያኔንና አምላኬን በተለያዩ ሥፍራዎች አገልግያለሁ:: ለትምህርት ወደ ዚምባብዌ ከመሄዴ በፊት በመሃከለኛው ሰበካ በወንጌላዊነትና በአስተማሪነት 7 ዓመት፣ ከሱሉስ (Soulsi) ዩንቨርሲቲ ከተመለስኩ በኃላ 3 አመት በፍልውሃ ቤተክርስቲያን በፓስተርነት፣ 5 አመት በኢትዩጵያ ዩንየን በዲፓርትሜንት ዳይሬክተርነት፣ 3 አመት በመሃከለኛው ኢትዩጵያ ሰበካ በኘሬዝዳንትነት፣ 4 አመት በኢትዩጵያ ዩንየን በዋን ፀሐፊነት፣ 7 ወራት በኢትዩጵያ ዩንየን በተጠባባቂ ኘሬዝዳንትነት አገልግያለሁ:: በእነዚህ ቦታዎች ሁሉ ጌታ ከእኔ ጋር በመሆን በሥራዬ ክንውንነትን ሰጥቶኛልና ከልቤ ላመሰግነው እወዳለሁ:: በአሁኑ ወቅት ደግሞ ጌታን በበለጠ እንዳገለግል እንደ ጌታ ፈቃድ ለሚቀጥሉት 5 አመታት በኢትዩጵያ ዩንየን ኘሬዝዳንትነት ተመርጫለሁ:: እስከዛሬ የረዳኝን ጌታን ተስፋ በማድረግ በአለፈው ሣምንት ይህንን ታላቅ ሃላፊነት በእምነት ተቀብያለሁ:: ጌታ የሥራው ባለቤት ስለሆነ እሱ በሚመራኝ መንገድ የተለመደውን አገልገሎቴን ለመስጠት ዝግጁ ነኝ::



***በኢትዮጵያ ዩንየን ባለፉት አምስት የሥራ አመታት ስለነበረው የአገልግሎት ውጤት እስቲ በአጭሩ ንገረን?***

በኢትዩጵያ ዩንየን በአለፉት 5 አመታት ጌታ ታላላቅና ድንቅ ሥራዎችን ሠርናአል::

1) በኢትዩጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በ5 አመታት ውስጥ ከ30000 ነፍሣት በላይ ጌታን ተቀብለዋል:: በተለይም በ2004 አመተ ምህረት ወደ 12000 ነፍሣት በጥምቀት ወደዚች ቤተ ክርስቲያን ተቀላቅለዋል::
2) ብዙ ወጣቶች በተለያዩ የትምህርት ዘርፎች ተመርቀዋል:: በተለይ በሥነ መለኮት ትምህርት ከ40 በላይ በዲኘሎማና በዲግሪ ተመርቀው የተለያዩ ፊልዶችን በማገልገል ላይ ይገኛሉ:: አሁንም በመሰልጠን ላይ ያሉ ከ30 በላይ ናቸው፣ይህ እጅግ ታላቅ ተግባር ነው:: እነዚህ ወጣቶች (አገልጋዩች) በቤተክርስቲያንችን ከፍተኛ ለውጥ እንደሚያመጡ እተማማናለሁ::
3) ከምንም ጊዜ በላይ በዛ ያሉ አብያተ ክርስቲያናትና ትምህርት ቤቶች የተሠሩበትና የተቋቋሙበት አመታት ያለፉት 5 አመታት ናቸው::

***በኢትዩጵያ ውስጥ ባሉት አምስት ፊልዶች እየተስፋፋ ያለው የቤ/ክ አገልግሎት በጣም የሚያስደስት ነው፣አንዳንድ ሃይላይቶችን ለአንባቢያን ብትዘረዝርልን?***

ከላይ በአንደኛው ቁጥር የተጠቀሱት በሁሉም ፊልዶች የተከንወኑ ተግባራት ናቸው:: በተለይ መሃከለኛው ሰበካ በ1ኛነት ደረጃ የተንቀሣቀሰ ሲሆን ምዕራብ፣ ደቡብ፣ ሰሜን ምዕራብን ትግራይ ሚሽንም ከፍተኛ እነቅስቃሴ አድርገዋል ::

***የፈቃደኛ ወንጌላውያንን ሚና በኢትዩጵያ እንዴት ታየዋለህ?***

የፈቃደኛ ወንጌላዊያን ሚና በኢትዩጵያ ከቀን ወደ ቀን ፣ ከሣምንት ወደ ሣምንት፣ ከወር ወደ ወር፣ ከአመት ወደ አመት፣ እያደገና እየጠነከረ መጥቶአል:: ፈቃደኛ ወንጌላዊያን ለፊልዱ እንቅስቃሴና እድገት የጀርባ አጥንት ናቸው:: ዋናው ሥራ የተከናወነው በእነሱ ስለሆነ በእኔ አይን ለዚህ ሁሉ ስኬት (ክንውን) ከፍተኛ አስተዋፅዎ አድርገዋል:: ምዕመናን በመክሊታቸው፣ በገንዘባቸው፣ በእውቀታቸውና በግዜያቸው በታማኝነት ጌታን እያገለገሉ መሆንቸውን ነው የማውቀው:: ስለሆነም ለዚህ ሁሉ ውጤት መመስገን አለባቸው::

***የ58ኛው የጀኔራል ኮንፈራንስ ስብሰባ ተወካይ ሆነህ ተገኝተህ ነበር፣ በነዚህ 10 ቀናት ውስጥ ካየሃቸውና ከሰማሃቸው ነገሮች የነበረህን ኢምኘሬሽን ለአንባቢያን ብትለን ?***

የ58ኛው የጀነራል ኮንፈራንስ ስብሰባ ከምንም ጊዜ የተለየ የሚያደርጉት ባህርያቶች እንደነበሩ ተረጅቻለሁ:: እስከዛሬ እኔ የተካፈልኩት ሁለት ጊዜ ብቻ ስለሆነ ብዙ መናገር ባልችልም ከሰማሁትና ከአየሁት ጥቂት ማለት እሻለሁ:: የ58ኛው የጀኔራል ኮንፈራንስ ስብሰባ ከሌሎች ከሚለይባቸው ምክንያቶች አንዱን ዋነኛው መንፈሣዊነት የታየበት፣ ሰላምና መግባባት የሰፈነበት፣ ሰዎች በፀሎት ከምንም ጊዜ ይልቅ የተጉበት፣ ታላላቅ መንፈሣዊ በረከቶች የታዩበት፣ ብዙዎች በአሉበት ቦታ በድጋሚ የተመደቡበትና ሰላማዊ የሆነ ስብሰባ ነበር:: እኔ ደግሞ ቤተክርስቲያኔን በበለጠ የወደድኩበትና የአከበርኩት ወቅት ነበር::

***አለም አቀፍ አድቬንቲስት ቤ/ክ የአምስት አመት የስራ ሪፓርት በተመለከተ ምን ለየት ያሉ ዜናዎች ነበሩ? በስብሰባው ላይስ ምን ምን ውሳኔዎች ተወሰኑ?***

አለም አቀፍ ቤተክርስቲያን በሚመለከት በአለፉት 5 ዓመታት ብዙ ነፍሣት ወደ አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን የተጨመሩበት አመት ነበር:: ግሎባል ሚሽንና የአድቬንቲስት አለም አቀፍ ሬድዮ ጣቢያ ያስገኙት ድንቅ ለውጥን እድገት የተለየ ትኩረት የተሰጠው ነበር:: በስብሰባዎች ላይ የተወሰኑ ውሣኔዎች በዛ ያሉ ሲሆኑ እኔ የመራጭ ኮሚቴ አባል ስለነበርኩ በአብዛኛው ውሣኔ ላይ አልነበርኩም:: ዋናውና ትልቁ አድቬንቲስት ቤ/ክ 28ኛውን መሠረታዊ እምነት ጨምራለች::

***ኢትዮጵያ ዩንየን ወክላችሁ የመጣችሁት ደልጌቶች በአሜሪካ ውስጥ የሚገኙትን ኢትዩጵያውያን አድቬንቲስት አባሎች አግኝታችሁ ተሰብስባችሁ ነበር? የስብሰባችሁ አላማና እቅድ ምንድን ነበር?***

በአሜሪካን ውስጥ የሚኖሩትን ኢትዩጵያውያንን ቀደም ብዬ በኢሜል አማካኝነት ከሁለት ወር በፊት ላነጋግራቸው እንደምፈልግ አድራሻቸው ለአለኝ ሰዎች ሁሉ መልእክት አስተላልፌ ነበር:: ዋናው አላማው: በኢትዩጵያ የሚሠራውን ሥራ ለሁሉም ለመግለፅ፣ ስለ ሃገራቸው መንፈሣዊ እንቅስቃሴና እድገት በበለጠ እንዲያውቁ ለማድረግ ሲሆን፣ በተጨማሪም ለወደፊቱ በሥራው እንዲሣተፉ ለማነሣሣት ነበር:: ማለትም በፀሎት፣ በምክርን ሃሣብን በማካፈል የተለያዩ መክሊቶቻቸውን በመጠቀም ለሀገራቸው መንፈሣዊ እድገት አስተዋፅዎ እንዲያደርጉ ለማደፋፈር ነበር::

***በውጭ አገር የሚገኙ ወጉች በኢትዩጵያ ውስጥ ያለውን የወንጌል ስርጭት እንቅስቃሴ በምን አይነት መንገድ ሊደግፉ ይችላሉ?***

በውጭ ሀገር ያሉ ኢትዩጵያዊያን ሀገራቸውን ሊደግፉ የሚችሉት በብዙ መንገድ ነው:: በፀሎት፣በምክር፣በገንዘብ፣ በሙያና በተለያዩ መንገዶች የወንጌልን ሥርጭት ሊደግፉ ይችላሉ::

***በወቅቱ በእቅድ ላይ የሚገኙ የኢትዮጵያ ዩንየን ኘሮጀክቶችን ዝርዝር ብትገልጽልን?***

በወቅቱ በእቅድ ላይ ያሉ ኘሮጀክቶች፣ 1) የተለያዩ መንፈሣዊ ፅሁፎችን ማሣተም፣ 2) የተተረጐሙ የትንቢት መንፈስ ፅሁፎችን ማሣተም፣ 3) የውዳሴ መዝሙር መጽሐፍ ማሣተም፣ 4) ያለብንን የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት ለመቅረፍ በተለያዩ ዘርፎች ማሰልጠን፣ 5) በኢትዩጵያ ዩንየን መግቢያ በር ላይ የመጽሐፍ፣ የመዝሙር ካሴቶችንና የተለያዩ መንፈሣዊ ፅሁፎችን የምናሠራጭበት መጽሐፍ ቤት መሥራት፣ 6) የፅሁፍ ወንጌላዊያንን ማሰልጠን፣ 7) የህትመት እንቅስቃሴያችንን ከዚህ በፊት በተለየ ሁኔታ ማሣደግ ናቸው::

***በሚቀጥለው አምስት የስራ አመታት የኢትዩጵያ ዩንየን እቅድና ራእይ ምንድን ነው?***

የኢትዩጵያ ዩኒየን ራሱን እንዲችል ማድረግ፣ ፊልዶች ሁሉ እራሣቸውን እንዲችሉ ማሣደግ፣ቤተክርስቲያኒቱን ሊመሩ የሚችሉ ወጣናችን ማሠልጠን፣ የወንጌል እንቅስቃሴ አሁን ከአለበት በእጥፍ ማሣደግ ፣ በብዙ ከተማዎች ት/ቤትን ቤተ ክርስቲያንት መሥራት፣የመጋቢነት ትምህርት አባላት በደንብ እንዲያውቁ ማድረግ፣ ምዕመንን በቤተክርስቲያን እንቅስቃሴ ከዚህ በፊት በተሻለ ሁኔታ ማሣተፍ፣ በመንግስት የተወረሱ ሆስፒታሎቻችንን ማስመለስ፣የሬድዩ ሥርጭታችንን ማጠንከር፣በኦሮሚኛ፣በትግሪኛ፣ በአፋርኛና በአማርኛ የሚተላለፈውን መልእክት ለሰዎች ሁሉ ይዳረስ ዘንድ የተለየ ጥረት ማድረግ ናቸው::

***ፓስተር አለሙ ለቃለ መጠይቅ ጊዜህን ስለሰጠኸን የትንቢት ቃል በአንባቢያን ስም ሆን ምስጋና ታቀርባለች::***

እኔም ከልብ አመሰግናለሁ:: እግዚአብሔር ይባርካችሁ:: ◆





# የኤች.አይ.ቪ.(ኤድስ) የምክር አገልግሎት (Counseling)

ኤች.አይ.ቪ. (ኤድስ) በማህበራዊ ኑሮ በስነልቦናዊና ኢኮኖሚያዊ ሕይወት ላይ መዛባትን ያስከትላል። ማለትም የሰዎችን የእርስ በርስ ማሕበራዊ ቁርኝነትን በማላላት ጥርጣሬና ፍርኃትን እያነገሰ የስጋትና የጭንቀት ምንክያት ሆኖአል። በአንድ የኤድስ በሽተኛ ላይ ሊፈጠሩ የሚችሉትን የአእምሮም ሆኑ ሌሎች ችግሮችን ማቃለል ወይንም ማስወገድ የሚቻለው የቅርብ ጓደኛን፣ ሐኪምን ወይንም ስለዚህ በሽታ ምክርን ሊሰጡ የሚችሉትን ድርጅቶችን በማማከር ይሆናል። እራስን ገለልተኛ አድርጎ መቀመጥ ለዚህ ችግር መፍትሔ ሊሰጥ አይችልም። ሕብረተሰብ ቤተሰብም ሆነ ግለሰብ የበሽታው ተጠቂዎችን በበጐ አይን በመመልከት እንዲረዳቸውና እንዲንከባከባቸው ተገቢውንም ድጋፍ እንዳይነፍጋቸው ሳይታክቱ ማስተማርና ግንዛቤ መፍጠር ያስፈልጋል።

ሕበረተሰባችን ስለበሽታውና ስለ በሽተኞቹ ያለው አመለካከት የጠራ እንዲሆን ያስፈልጋል። ይህ ማለትበተጠቂዎቹ ላይ የሚደርሰውን ከፍተኛ የመገለል ስሜትና የስነ ልቦና ችግር ለመቅረፍ በባለሙያና በጥናት የተደገፈ የምክር አገልግሎት መስጠት እጅግ አስፈላጊ ነው።

የካውንስሊንግ (የምክር) አገልግሎት የስነልቦናዊ መንፈሳዊ ማሕበራዊ ድጋፎችን የሚያጠቃልል ሲሆን የአግልግሎቱ ተጠቃሚዎች ላይ የፀባይ ለውጥ ለማምጣት ይረዳል። ስለዚህ የምክር አገልግሎት ስንል በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የማማከር አገልግሎት በመስጠት የሰዎችን ችግር ተገንዝቦ ለችግሮቻቸው የጋራ መፍትሔ ለማግኘት ጥረት ማድረግን ያመለክታል።

## የምክር አገልግሎት ጠቀሜታ

ግለሰቡ ለቫይረሱ የተጋለጠ መሆኑን ሲረዳ የሚፈጠርበትን ከፍተኛ ድንጋጤ፣ ግራ መጋባት፣ የመንፈስጭንቀት፣ ተስፋ መቁረጥና መሰል ስሜቶችን ተቋቁሞ ሕይወቱን ለማቀድ እንዲችል ለማገዝ ሲሆን ብቁ የምክር አገልግሎት ውጤቶች ደግሞ

- የቫይረሱ ሰለባ የሆኑ ሕሙማን ተስፋ እንዳይቆርጡና የመንፈስ ጥንካሬ እንዲኖራቸው ያደርጋል
- ከኤች.አይ.ቪ ቫይረስ ጋር ተስማምቶ በመኖር ሁኔታውን በፀጋ በመቀበል ለረጅም ጊዜ መኖር እንደሚችሉ እንዲያውቁ ይረዳል
- ሕሙማኑ ቀና ስሜቶችን እንዲያዳብሩ በመምከርና በማስረዳት የፀባይ ለውጥ እንዲያመጡና ቫይረሱን ወደ ሌላ ሰው እንዳያስተላልፉ ለማድረግ ያስችላል።
- ማዳን የማይቻለው ኤች.አይ.ቪን እንጂ በቫይረሱ ምክንየት የሚከሰቱት በሽታዎችን አክሞ ማዳን እንደሚቻል ያሳውቃል
- ትክክለኛ መድሀኒት አወሳሰድ ተምረው እራሳቸውን በመጠበቅ መኖር ከቻሉ በአሁኑ ወቅት በሚደረገው ምርምርና ጥናት አንድ ቀን ለበሽታው መድኃኒት ሊገኝ እንደሚችል ማሳሰብ
- በሽታው የሚያስገልል ሳይሆን እንደማንኛውም ሰው በሕብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት እንዳላቸው ለማስገንዘብ ይረዳል። ◆

***ከአዘጋጆች***

## *የመልካም ስጦታዎች* *(ከገጽ1 የዞረ)*

ለውጫዊ ውበት ብዙ ቦታ ይሰጣል። በገና እና በአዲስ አመት ወቅት ብዙ ሺ ዶላር ለማይጠቅሙ ነገሮች ይባክናል። እኛ ግን በእነዚህ የአመት በዓል ቀናት ያለንን ገንዘብ ለማይጠቅም ምግብ፣ለማይረባ ጌጣጌጥ ወይም ልብስ ከማባከን ይልቅ ለእግዚአብሔር ክብር እንድናውለው እድል ተሰጥቶናል። ክርስቶስም በምናደርገው ሁሉ ነገር ዋናውን ቦታ መያዝ ይኖርበታል።

ለልጆቻችንና ለዘመዶቻችን ልንሰጣቸው የምንችላቸው ጥቂት ገንዘብ ብቻ የሚያስወጡና ትልቅ ደስታን የሚሰጡ ጣእም ያላቸው ብዙ ስጦታዎች አሉ። ልጆችህ የምትሰጣቸው ስጦታ ለየት ያለ እንደሆኑ ሲመለከቱና ጥያቄ ሲፈጥርባቸው፣የማይረቡ ስጦታዎችን ሳይሆን ለእግዚአብሔር ክብር የሚጠቅሙ ስጦታዎችን እንደሰጠሃቸው ስታስረዳቸው ልዩ ትምህርት ማግኘት ይችላሉ። የልጆችህን አእምሮ አዲስ ወደ ሆነው ራስ ወዳድነት ወደሌለው አቅጣጫ (መንገድ) ምራቸው። ለአምላክም ስጦታ መስጠትን አስተምራቸው (አለማምዳቸው)።

## የገና ዛፍ ሊኖረን ይገባልን?

እግዚአብሔርን የሚያስደስተው እያንዳንዱ ቤ/ክ ቤተክርስቲያንን ለማቆም (ለማስተዳደር) የሚችል የተሟላ የስጦታ ዛፍ ቢኖራት ነው። «የገና ዛፍ በቤተክርስቲያናችን ልናቆም ተፈቅዶአልን?» የሚል ጥያቄ ያላቸው ደብዳቤዎች ደርሰውን ነበር። መልስ ስንሰጥ እንዲህ ብለናል፥- በቤተክርስቲያናችን ውስጥ መልካም መአዛ ያለው ለሁልጊዜ አረንጓዴ የሆነ ዛፍ ማስቀመጥ በመሠረቱ ምንም ኃጢያት የለበትም። ኃጢያት የሚሆነው ይህንን ለማድረግ የተነሳሳንበት ምክንያት (Motivation) እና በዚያ ዛፍ ላይ የሚንጠለጠለው የስጦታ አይነትና አጠቃቀም ነው። ዛፉ የፈለገውን ያህል ትልቅ መሆን ይችላል ይሁን እንጂ ቅርንጫፎቹ በጎነታችሁንና መልካምነታችሁን በሚያሳዩ ምልክቶች ይሸለም (ይሸብርቅ)። ይህ ነው ለእናንተ የገና ስጦታችሁ ሊሆን የሚገባው። ይህንን ስጦታችሁንም በጸሎት ቀድሱት። የምናከብራቸው የገና እና የአዲስ አመት በዓላት የእኛ እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው የሚጠቅሙ ሊሆኑ ይገባል። ለምሳሌ ያህል ብዙ ልጆች ያላቸው ቤተሰቦችን በመርዳትና በመደገፍ እግዚአብሔርን ማስከበር እንችላለን።

## በመልካም ስጦታዎች የተሞላ ዛፍ

ለእግዚአብሔር ለመስገድ ወደ ቤ/ክ የሚመጡትን ሰዎች ደስ ለማሰኘት ሲባል በቤተክርስቲያን ውስጥ የቆመውን አረንጓዴ ዛፍ ማንም «ይህ ኃጥያት ነው» ብሎ ሊናገር አይገባም። እንዲያውም ትልቅ በረከት ሊሆን ይችላል። ዋና ትኩረት መሰጠት ያለበት ግን «በጎ አድራጎት» በሚለው መንፈስ ላይ ነው። የጌታ የየሱስ ክርስቶስ ልደት በዓል ዝም ብሎ የመዝናኛ ጊዜ ሳይሆን በረከት የሞላበት የህብረት ጊዜ ሊሆን ይገባዋል። በአለም ላይ እንደሚታዩት በሰዎች ላይ መጥፎ ተጽእኖ እንደሚያስከትሉት አይነት ዝግጅቶች ሳይሆን መልካም ነገርን ለማቅረብና ለማሳየት የምንችልበት እንደዚህ አይነት ጥሩ አጋጣሚ ስላለን እኔ በበኩሌ ደስ ይለኛል።

## በደስታ አሳልፉት

እህቶቼና ወንድሞቼ፥- ይህንን አመት በዓል ከእግዚአብሔር እንደተሰጣችሁ ኃላፊነት መጠን አሰልቺ በሆነ መልኩ ሳይሆን በተቻላችሁ መጠን በተሟላ ሰማያዊ ደስታ አሳልፉት። የምትጋብዙአቸው እንግዶቻችሁ በሕብረተሰቡ ዝቅተኛ ደረጃ ያላቸው ሰዎችና ድሆች ለዚህ መልካምነታችሁ ከልብ እንደሚያመሰግኑአችሁ እርግጠኛ ነኝ።

በቤተክርስቲያናችን ውስጥ ያሉት ባለጸጋዎችም እግዚአብሔር ባበዛላቸው መጠን ስጦታንና መስዋእትን በመስጠት ለዚህ አመት በዓል በረከት አስተዋጽኦ ሊያደርጉ ይገባቸዋል። የእግዚአብሔርን ሥራ እና የእርሱን መንግሥት የሚያስፋፉትን ፍጹም ልዩ ስጦታዎችን በመስጠት በሰማይ መዝገቦች ውስጥ መቼም ተጽፎ እንደማይታወቅ አይነት ልዩ የልደት በዓል እናክብር። ◆

***ምንጭ***

***(The Adventist Home, page 477-483)***



# 144000 ዎቹ እነማን ናቸው?

በ ዳግ ባችለር

ይህንን አርእስት በምናጠናበት ጊዜ በተቀደሰ ጉዳይ ላይ ስለምንነጋገር ጥንቃቄ ያስፈልጋል። ምንም እንኳን ይህንን ሳቀርብ በሙሉ እምነት ቢሆንም ሌሎች ደግሞ የተለያዩ ትርጉሞች ሊሰጡት እንደሚችሉ አውቃለሁ።

የራእይ መጽሐፍ በመጨረሻው ጊዜ ታላቅ መንፈሳዊ ሥራ ስለሚያከናውኑ የተለዩ ኃይሎች ይናገራል። እነዚህ 144000 ሰዎች ምድርን ለክርስቶስ ዳግም ምጽአት ለማዘጋጀት ወሳኝ የሆነ መልእክት እና ከበጉ ጋር የተለየ ግንኙነት አላቸው። መዝሙራቸውም የተለየ ሲሆን በልዩ ስምም ታትመዋል። እነዚህ ቅዱስ ወታደሮች እነማን ናቸው? ለዚህ መልስ ለማግኘት አስቀድመን ስለእነሱ የተጻፋትን ሁለት የመ/ቅ ጥቅሶች እንመልከት። 1ኛ) ራእይ 7፥1-4 2ኛ) ራእይ 14፥1-5 (ውድ አንባቢ፥ በመጀመሪያ ጥቅሶቹን በግልዎ ያንብቡ)

## አስራ ሁለቱ ነገዶች

ከ ራእይ 7፥1-4 ቀጥሎ ያሉት ጥቅሶች 144000ዎቹ ከ12ቱ የእስራኤል ነገዶች ከእያንዳንዱ 12000 ሰዎች እንደተውጣጡ ይዘረዝራል። ስለዚህ አስቀድመን መጠየቅ የሚገባን ጥያቄ «እነዚህ 144000 ሰዎች በቀጥታ ከእያንዳንዱ የእስራኤል ነገድ 12000 ሆነው የተውጣጡ ናቸው ወይ?» የሚለውን ጥያቄ ነው።

በአንደኛ ደረጃ ከዚህ ቀደም የነበሩት ነገዶች 12 ሳይሆኑ 13 መሆናቸውን እናስተውል። 12ቱ ነገዶች የመጡት እግዚአብሔር ስሙን «እስራኤል» ብሎ ከሰየመው ከያእቆብ ልጆች ነው። ከያእቆብ ልጆች ውስጥ አንዱ (ዮሴፍ) ወንድሞቹ ወደባርነት ስለሸጡት ዮሴፍ ለረጅም አመታት ከቤተሰቡ ተለይቶ ኖረ። በመጨረሻ ዮሴፍ ወደአባቱ ከተመለሰ በኋላ ያእቆብ የዮሴፍን ሁለት ልጆች እንደራሱ ልጆች ቆጥሮ ስለወሰዳቸው የዮሴፍ ቦታ በሁለት ልጆቹ ተተካ። ከዚያም ዮሴፍ በልጆቹ በኩል እንደሁለት ተቆጠረ (ዘፍ 48፥5)። በመላው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ 12 ነገዶች ብቻ የሚጠቀሱበት አንዱ ምክንያት የሌዊ ነገድ የእስራኤል ካህን እንዲሆን ሲመረጥ የውርስ ቦታ ግን እንዳይሰጠው ስለተደረገ ነው (ዘዳ 10፥8-9 ዘዳ 18፤1)። በተጨማሪም የሌዊ ነገድ በሕዝብ ቆጠራ ውስጥ እንዳይሳተፍ ተደረገ (ዘሁ 1፥49)። በአንጻሩ ግን የሌዊ ነገድ የሁሉም ነገዶች ካህናትና አስተማሪ ሆነ።

በራእይ 7 ላይ የተጠቀሱት ነገዶች በቀጥታ የቀድሞዎቹ የእስራኤል ነገዶች እንዳልሆኑ የሚገልጹ ብዙ ምክንያቶች አሉ። ከ12ቱ የእስራኤል ነገዶች ውስጥ 10ሩ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ722 ም.ዓ. በአሶራዊያን ተማርከው እንደተወሰዱ ለረጅም አመታትም ተበታትነውና ከአህዛብ ጋር ተጋብተው (ተዳቅለው) እንደኖሩ ብሉይ ኪዳንና ታሪክ ይገልጻል (2ኛ ነገ17፥6)። እንግዲያስ በራእይ ውስጥ የተጠቀሱት 144000ዎቹ የተውጣጡት ከየት ነው? በእኔ እምነት የዚህ ጥያቄ መልሱ «እግዚአብሔር ለጥንቱ እስራኤል የሰጠው ተስፋ ዛሬ በመንፈሳዊው እስራኤል ይፈጸማል» የሚለው ነው። ከክርስቶስ ልደት ከ34 ዓ.ም. በኋላ ትንቢትና የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል የሚያተኩረው አይሁድም ሆነ አህዛብ አንድ ሰው በእምነት የእግዚአብሔር ልጅ በመሆኑ ላይ ነው (ሮሜ 2፥28-29 ገላ3፥29)።

## በስም ውስጥ ምን አለ?

የ144000ዎቹ ሰዎች ስም መንፈሳዊ ትርጉም እንዳለው ከሚያመለክቱቱ ነጥቦች ውስጥ አንዱ የእነዚህ ነገዶች ስም በራእይ 7፥5-8 እንዴት እንደተጠቀሱ ስንመለከት ነው። የነገዶቹ ስሞች በዚህ ቅደም ተከተል የተጠቀሰው በዚህ ጥቅስ ውስጥ ብቻ ነው። ማለትም የያእቆብ የመጀመሪያ ልጅ ሩባን የተጠቀሰው በሁለተኛ ደረጃ ሲሆን አራተኛው ልጅ ይሁዳ ደግሞ በመጀመሪያ ደረጃ ነው የተጠቀሰው። እዚህ ቦታ ዮሴፍና ሌዊም ሲጠቀሱ ኤፍሬምና ዳን ደግሞ ሳይጠቀሱ ቀርተዋል። ለምን?። ምክንያቱን በዘፍ 49፥17 እና ሆሴእ 4፥17 ይመልከቱ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እባብ የሰይጣን ምሳሌ ነው። የዳን የከሳሽነትና የሀሜት ተፈጥሮ የእርሱን ነገድ ከእግዚአብሔር መንግሥት ጋር ሳይሆን ከሰይጣን መንግሥት ጋር አመሳስሎታል። የኤፍሬም ነገድም የእስራኤል አምላክን በመተው ወደ ጣኦት አምልኮ ዞር አለ። ለዚህም ነው ኤፍሬምና ዳን ከ144000ዎቹ ውስጥ ያልተጠቀሱት።

በአይሁዶቹ ባህል መሠረት ልጅ ሲወለድ የሕጻኑን ባህርይ ወይንም ከመወለዱ ጋር ከተያያዙ ክስተቶችጋር የተገናኘ ትርጉም ያለው ስም ይወጣለታል። ለምሳሌ ዘፍ 29፥32-35 ማየት ይቻላል። እንዲያውም ራሄልና ሊያ ለአስራሁለቱ የያእቆብ ልጆች ትንቢታዊ አነጋገር ተናግረዋል ማለት ይቻላል። ከዚህ በታች 144000ዎቹ የተውጣጡባቸው ነገዶች ስሞች ልክ በራእይ 7 እንደተዘረዘረው ቅደም ተከተል ከነትርጉማቸው ተገልጸዋል። ይሁዳ (እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ)፤ሮቤል (እግዚአብሔር መከራዬን አይቶአል)፤ጋድ (መልካም እድል ሆነልኝ)፤አሴር (ደስታ ሆነልኝ)፤ንፍታሌም (ታገልኩ አሸነፍኩም)፤ምናሴ (እንድረሳ አደረገኝ)፤ስምኦን (እግዚአብሔር ሰማኝ)፤ሌዊ (ወደ እኔ ይጠጋል)፤ይሳኮር (ዋጋዬን ሰጠኝ)፤ ዛበሎን (ከእኔ ጋር ይኖራል)፤ዮሴፍ (እግዚአብሔር ይጨምርልኝ)፤ብንያም (የቀኙ ልጅ) ። የእነዚህ ስሞች ትርጉም በአንድነት ቢዋሃድና ቢነበብ ልዩ ትርጉምን ይሰጠናል። የእነዚህ ስሞች ትርጉም የቤተክርስቲያንን የትግል፤የመዳንና የድል ታሪክ ያስረዳሉ።

## ስንት ናቸው ?

የሚቀጥለውን ዋና ጥያቄ ደግሞ እስቲ እንመልከት። «144000» የሚለው ቁጥር ምሳሌያዊ ነውን? ይህንን ጥያቄ በጥያቄ መመለስ እችላለሁ። ሌሎቹ በራእይ ውስጥ የተጠቀሱት ቁጥሮች ቃል በቃል የሚወሰዱ ናቸው ወይስ ምሳሌያዊ? በቅድስቲቷ ከተማ የሚኖሩት 12 በሮችና 12 መሠረቶች ብቻ ናቸው? በሕይወት ዛፍ ላይስ 12 የተለያዩ ፍሬዎች ብቻ ነው ያሉት? የሁሉም መልስ «አዎን በርግጥ» የሚል ነው። በአዲሲቷ የሩሳሌም ውስጥ ስላለው መጠን የምንገምተው ነገር ሁሉ እነዚህ ቁጥሮች ትክክለኛ ናቸው ብለን የምናምነውን ያህል ነው።

ምንም እንኳን 144000 ምሳሌያዊ ሳይሆን ቃል በቃል የሚወሰድ ቁጥር ቢሆንም እነዚህ ሰዎች እነማን እንደሆኑ ለይቶ ለማወቅ ግን ለሰዎች ጭራሽ የማይቻል ነው። የሱስ ምድር ላይ በነበረበት ጊዜ የሚቀርቡትን 12ቱን ተከታዮቹን እነማን እንደሆኑ ማወቅ አስቸጋሪ አልነበረም። በመጨረሻው ጊዜ የሚኖሩት 144000 ግን መንፈሳዊ አይሁዳዊያን ሲሆኑ በተለያዩ የምድር ክፍሎች ተበታትነው ታላቅ የተሃድሶ መነቃቃትን የሚመሩ ናቸው። ምናልባት አንዳንዶች «እንዴት 144000 ቃል በቃል የሚወሰድ ቁጥር፤ሰዎቹ ግን ምሳሌያዊ ሊሆኑ ይችላሉ?» ብለው ያስቡ ይሆናል። የሱስ 12 ደቀመዛሙርቱን ሲመርጥ ከየትኛው ነገድ እንደሆኑ ጭራሽ ግድ አልሰጠውም ነበር። እነዚህን ሰዎች ሲመርጥ ግን የራሱ አላማ ነበረው። እዚህ ላይ ማስታወስ የሚገባን ሌላ ነገር ደግሞ ሁሉም በራእይ ውስጥ የተጠቀሱት ቁጥሮች የሚያሳዩት የተወሰነ መጠንን ሲሆን የሰዎች ስሞች ደግሞ በራእይ መጽሐፍ የምሳሌ አነጋገር ናቸው (ለምሳሌ በግ፤ዘንዶ፤አንበሳ፤በለአም፤ኤልዛቤል ....)።

ከዚህና ይህንን ከመሳሰሉት ምክንያቶች የተነሳ እኔ 144000 ቁጥር ምሳሌያዊ ሳይሆን ቃል በቃል የሚወሰድ ቁጥር እንደሆነ አምናለሁ። ልክ በብሉይ ኪዳንም 12 ቃል በቃል የሚወሰዱ ነገዶች፤በአዲስ ኪዳንም 12 ቃል በቃል የሚወሰዱ ደቀመዛሙርት እንደነበሩ፤በመጨረሻው ጊዜም 12 ጊዜ 12000 መንፈሳዊ ደቀመዛሙርት (ሐዋሪያት) ይኖራሉ።

«ይህ ቁጥር ቃል በቃል የሚወሰድ ከሆነ የሚድኑቱ 144000 ብቻ ናቸው ወይ?» ብለው የሚጠይቁ ብዙዎች ናቸው። «እንደዚህ ከሆነ የእኔ የመዳን እድል ምን ያህል ነው?» ይላሉ። መጽሐፍ ቅዱስ «የሚድኑት ሰዎች 144000 ብቻ ናቸው» አይልም። በራእይ 7 ውስጥ 144000ዎቹ ከተጠቀሱ በኋላ ነቢዩ ወዲያውኑ «አንድ እንኳን ሊቆጥራቸው የማይችል ከሕዝብና ከነገድ ከወገንም ከቋንቋም ሁሉ እጅግ በዙ ሰዎች ነበሩ፤ነጭ ልብስም ለብሰው የዘንባባም ዝንጣፊዎች በእጆቻቸው ይዘው በዙፋኑና በበጉ ፊት ቆመው አየሁ» ይላል (ራእይ 7፥9)። በቁጥር 13 ላይም ከ24ቱ ሽማግሌዎች ውስጥ አንዱ «እነዚህ ነጩን ልብስ የለበሱት እነማን ናቸው? ከወዴትስ መጡ?» ብሎ ዮሐንስን ይጠይቀዋል። ዮሐንስም «እነዚህ ከታላቁ መከራ የመጡ ናቸው፤ልብሳቸውንም አጥበው በበጉ ደም አነጹ» በማለት መልስ ይሰጣል። የመጽሐፍ ቅዱስ የትንቢት ቃል ሁለት ታላላቅ የስደት (የመከራ) ጊዜያት እንዳሉ ይናገራል። አንደኛው በጳጳስ ስርአት ዘመን በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ክርስቲያኖች ያለቁበት ጊዜ ሲሆን፤ዋናው ስደት ደግሞ የሱስ ዳግም ከመምጣቱ በፊት ያለው ነው። ይህም በዳንኤል 12፥1-2 ተጠቅሶአል።

## ተልእኮአቸው

144000ዎቹ በቤ/ክ ታሪክ የመጨረሻ ጊዜ የሚሠሩ ሲሆኑ የቀድሞዎቹ ደቀመዛሙርት አይነት ልምምድ ይኖራቸዋል። የሱስ በመጀመሪያ ጊዜ ወደ ምድር ሲመጣ የመረጣቸው 12 ደቀመዛሙርት አቢይ ተልእኮአቸው ወደ እስራኤላውያን ነበር። የቀድሞው (የመጀመሪያው) ዝናብ በዘነበ ጊዜም በጴንጤቆስጤ ቀን ደቀመዛሙርቱ በበዙ ሺህ ለሚቆጠሩ ነፍሳት መመስከር ቻሉ (ማቴ 10፥5-6 ይመልከቱ)። በመጨረሻ ጊዜም የሱስ 144000 መንፈሳዊ ደቀመዛሙርትን በመጠቀም ምድርን ለዳግም ምጽአቱ ያዘጋጃታል። በራእይ 7 ላይ የተጠቀሱት ሊቆጠሩ የማይችሉ ብዙ ነፍሳት የመጨረሻው (የኋለኛው) ዝናብ ሲወርድ 144000ዎቹ መንፈሰዊ ደቀመዛሙርት በመንፈስ ቅዱስ በመሞላት በሚሰጡት ምስክርነት የዳኑ ናቸው። ነበዩ ኢዩኤል ስለነዚህ ክስተቶች አስቀድሞ ተናግሮአል (ኢዩኤል 2፥28-29)።

በመጨረሻው ዘመን ወንጌልን የሚሰበኩ 144000ዎቹ ብቻ እንዳልሆኑ መዘንጋት አያስፈልግም። አስራሁለቱ ደቀመዛሙርት ከ120 የጌታ ተከታዮች ጋር በበአለ ሃምሳ ቀን መንፈሳዊ መነቃቃት የመሩ እንደመሆናቸው መጠን 144000ዎቹም በመጨረሻው ዘመን የመነቃቃት መሪዎች ናቸው እንጂ ሰበኪዎቹ እነርሱ ብቻ አይደሉም። የሱስ 12 ደቀመዛሙርቱን ከካህናት መሃል ሳይሆን ከተራው ህዝብ መምረጡም አተኩሮ የሚሰጠው ነጥብ ነው። በዚሁም መንገድ 144000ዎቹ የተውጣጡት ከቤ/ክ አገልጋዮች ብቻ አይሆንም፤እንዲያውም አብዛኛዎቹ ከፈቃደኛ አገልጋዮች (ሌዩቲ) የተውጣጡ ናቸው ብዬ አምናለሁ።

የሐዋሪያት ሥራ ምእራፍ አንድ ላይ መንፈስ ቅዱስ እንደቀድሞው (መጀመሪያው) ዝናብ ከመውረዱ በፊት የተከሰቱትን ክስተቶች አስገራሚ በሆነ ቅደምተከተል እንደነበረ ይገልጻል፥- በመጀመሪያ ደቀመዛሙርቱ ልባቸውን ሙሉ በሙሉ ወደ የሱስ አቀኑ (ቁ.10-11)። ከዚያም ጸለዩ፤በመካከላቸው ያለውንም ልዩነት አስወገዱ (ቁ.13-14)። በመጨረሻም የሞተውን ደቀመዝሙር እንዲተካ ማቴዎስን መረጡ (ቁ.16-26) ። የደቀ መዛሙርቱ ቁጥር 12 ከሞላ በኋላ በላይኛው ክፍል በአንድነት ተቀምጠው ሳሉ መንፈስ ቅዱስ ወረደላቸው (ምእ.2)። በአሁኑ ወቅትም የሱስ የእግዚአብሔርን ልጆች ወደ ንስሃ የሚመሩትን የተለዩ ኃያላትን እያሰለጠነ ነው። ራእይ 14፥4 ስለ 144000ዎቹ ሲያውጅ እንዲህ ይላል «ከሴቶች ጋር ያልረከሱ እነዚህ ናቸው፤ድንግሎች ናቸውና። በጉ ወደሚሄድበት የሚከተሉት እነዚህ ናቸው»። በጉን ለዘላለም ከሚከተሉት መሃከል ለመሆን አስቀድመን እርሱን እዚሁ መከተል መማር አለበን። ከዚያም በአንድነት የሙሴን እና የበጉን መዝሙር መዘመር እንችላለን።◆



# የመከራ ዘመን (ክፍል 1)

ታላቁ ተጋድሎ ምዕ.39

ውድ የትንቢት ቃል አንባቢያን፥ ካለፉት እትሞች ጀምሮ «The Great Controversy» ወይም «ታላቁ ተጋድሎ» ከሚለው መጽሐፍ ውስጥ የመጨረሻዎቹን ሰባት ምእራፎች በተከታታይ በማቅረብ ላይ ነን። ይህ መጽሐፍ በ19 መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ እና በ20 መቶ ክ.ዘ. መጀመሪያ ላይ በ ኤለን ጂ ኋይት የተጻፈ ሲሆን ወቅታዊ እውነትንና ትንቢትን የያዘ በመሆኑ ለአንባቢያን በረከት ይሆናል ብለን በማሰብ ካለፈው ቀጣዩን መልእክት ይዘን ቀርበናል።

«በዚያም ዘመን ስለ ሕዝብህ ልጆች የሚቆመው ታላቁ አለቃ ሚካኤል ይነሣል፤ ሕዝብም ከሆነ ጀምሮ እስከዚያ ዘመን ድረስ እንደ እርሱ ያለ ያልሆነ የመከራ ዘመን ይሆናል፤ በዚያም ዘመን በመጽሐፉ ተጽፎ የተገኘው ሕዝብህ ሁሉ እያንዳንዱ ይድናል»(ዳንኤል 12፥1)። የሶስቱ መላእክት መልእክት ተሰራጭቶ ካለቀ በኋላ ኃጢያተኛ ለሆኑት ለምድር ነዋሪዎች የክርስቶስ ጸጋ ያበቃል፤፤ የእግዚአብሔር ሕዝብ ተልእኮዋቸውን (ሥራቸውን) አሟልተው ፈጽመዋል፤፤ የእግዚአብሔር ሕዝብ «ኋለኛውን ዝናብ» እና «ከጌታ ፊት መጽናናትን» ተቀብለዋል፣ ለሚጠበቃቸው የፈተና ጊዜም ተዘጋጅተዋል። መላእክትም በሰማይ ወዲህ ወዲያ እያሉ ይሯሯጣሉ። ከምድር የተመለሰው አንዱ መልአክ ሥራውን እንዲፈጽም፣ የመጨረሻውም ፈተና በአለም ላይ እንደጀመረ እና ለመለኮታዊ ትእዛዛት ታማኝ የነበሩ ሁሉ «የሕያው አምላክን ማህተም» እንደተቀበሉ አስታወቀ (አወጀ)።

ከዚያም የሱስ በሰማይቱ ቤተመቅደስ ያከናውን የነበረውን የማማለድ ሥራ ያቆማል። እጆቹንም ወደ ላይ ከፍ አድርጎ በታላቅ ጩኸት «ተፈጸመ!» ሲል ይናገራል። «አመጸኛው ወደፊት ያምጽ፣ እርኩሱም ወደፊት ይርከስ፣ ጻድቁም ወደፊት ጽድቅ ያድርግ፣ ቅዱሱም ወደፊት ይቀደስ» (ራእ 22፣11) ብሎ ሲያውጅ የመላእክት ሠራዊት ሁሉ ዘውዶቻቸውን አንስተው ያስቀምጣሉ።

የእያንዳንዱ ሰው ጉዳይ ወይ ለሕይወት ወይም ደግሞ ለሞት ተወስኖአል። ክርስቶስ ለሕዝቡ የሚያደርገውን የእርቅ ሥራ ፈጽሞ አል። ኃጢያቶቻቸውንም ደምስሶአል። የተገኘዎቹ ቁጥርም ተወስኖአል። «መንግሥት፣ ኃይልና ከሰማያት በታች ያለው ስልጣን ሁሉ ለዳኑት ይሰጣል፤ የሱስም የነገሥታት ንጉሥ እና የጌቶች ጌታ ሆኖ ይነግሣል። ኃጢያተኞች የምህረት ገደባቸውን አሳልፈዋል። ወደ ንስሃ ሲመራቸው ባለማቋረጥ ሲቃወሙት የነበረው የእግዚአብሔር መንፈስ በመጨረሻ ከእነርሱ ይወሰዳል። በመለኮታዊ ጸጋ ስላልተጋደሉ ለክፋው የተጋለጡ ይሆናሉ። ከዚያም ሰይጣን በምድር የሚኖሩትን ወደ መጨረሻው ታላቅ የመከራ ዘመን ይመራቸዋል። የእግዚአብሔር መላእክት አግደው ይዘው የነበሩትን ኃይለኛ ነፋሳት በሚለቅቁበት ጊዜ የህውከትና የብጥበጥ ኃያላት (ሥልጣናት) ይፈታሉ። ይህች አለም በጥንቲቱ እየሩሳሌም ከደረሰው ጥፋት ወደሚበልጥ አሰቃቂ ጥፋት ትገባለች። አንድ መልአክ ብቻውን የግብጻዊያንን በኩር ልጆች ሁሉ አጠፋ፣ ምድሪቱንም በሃዘን አጥለቀለቃት። ንጉሥ ዳዊትም ሕዝቡን በመቁጠሩ ምክንያት በእግዚአብሔር ፊት በበደለ ጊዜ ሃጢያቱ የሚቀጣበትን አሰቃቂ ጥፋት አንድ መልአክ ብቻውን ሊያመጣ ቻለ። ያ በእግዚአብሔር ትእዛዝ መሰረት ቅዱሳን መልእክት ይሰሩበት የነበረው የማጥፋት ኃይል ጌታ ራሱ በሚፈቅድበት ጊዜ ደግሞ በክፉ መላእክት ይከናወናል። በየቦታው ታላቅ ጥፋትን ለማስከተል የእግዚአብሔርን ፈቃድ በቻ በመጠባበቅ የተዘጋጁ ኃይሎች ዛሬም አሉ።

የእግዚአብሔርን ሕግ የማያከበሩት ሰዎች «በአለም ላይ ፍርድን ያመጣችሁት እናንተ ናችሁ!» በመባል ይከሰሳሉ። «ብጥበጥ፣ ደም መፋሰስ ያመጣችሁት እናንተ ናችሁ!» ተብለው በሐሰት ይወነጀላሉ። የመጨረሻውን ማስጠንቀቂያ አጅቦ የነበረው ኃይል ኃጢያተኞችን አስቆጣቸው፣ ቁጣቸውም መልእክቱን በተቀበሉት ሁሉ ላይ ነድዶአል። ሰይጣንም በበለጠ የጥላቻና የስደት መንፈስን በማጋጋል ሥራውን ይቀጥላል።

**የእግዚአብሔር መላእክት አግደው ይዘው የነበሩትን ኃይለኛ ነፋሳት በሚለቅቁበት ጊዜ የህውከትና የብጥበጥ ኃያላት ይፈታሉ።**

ያኔ እግዚአብሔር ከአይሁድ ሕዝቦች በመጨረሻ ራሱን ባገለለበት ወቅት ካህናትም ሆነ ሕዝቡ ይህንን አላስተዋሉም ነበር። በሰይጣን ቁጥጥር ስር ቢሆኑም፣ በጣም መጥፎና አሰቃቂ በሆነው ንዴታቸው ቢነዱም ቅሉ ራሳቸውን «እኛ የእግዚአብሔር ምርጥ ሕዝብ ነን» እያሉ ይሸነግሉ ነበር። በቤተመቅደስ ያደርጉ የነበረውንም አገልግሎት ይቀጥሉ፣ መስዋእቶቸቸውንም በረከሱት መሰውያዎቻቸው ላይ ይሰዉ፣ በየቀኑም የእግዚአብሔር ልጅ ክቡር ደም በፈሰሰውና የእርሱን አገልጋዮችና ሐዋሪያት ለመግደል በሚሻው ሕዝብ ላይ መለኮታዊ በረከት እንዲፈስስ ይለምኑ ነበር ። እንዲሁም ዛሬም በሰማይ ቤተመቅደስ ውስጥ የማይሻረው ውሳኔ በሚተላለፍበትና የአለም የመጨረሻ እጣ ለዘላለም በሚወሰንበት ጊዜም የምድር ነዋሪዎች ይህን ሳያስተውሉ ይቀራሉ። የእግዚአብሔር መንፈስ የራቃቸው ሰዎች የአምልኮ መልክ (ሃይማኖታዊነት) ይታይባቸዋል። በጥላቻ የተሞላው፣ አላማው ይከናወን ዘንድ እሱን ለሚከተሉት ሰዎች የሚሰጣቸው ሰይጣናዊ ቅንአት እንደ እግዚአብሔር ቅንአት መስሎ ይቀርባል።

ሰንበት በመላው የክርስቲያን አለም አጨቃጫቂ ነጥብ ስለሆነ ሃይማኖታዊና አለማዊ ባለስልጣናት እሁድ ቀን እንዲከበር ሲተባበሩ፤ በቁጥር እጅግ ጥቂት የሆኑት ይህንን ግዳጅ ለመቀበል ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ይህ ውሳኔአቸው ለጥላቻ የተዳረጉ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል። የቤተክርስቲያንን ስርአትና የመንግሥትን ሕግ የሚቃወሙት ጥቂት ሰዎች በትእግስት ሊታለፉ እንደማይገባቸው ጥብቅ ማሳሰቢያ ይወጣል። ይህም «መላው ሕዝብ ተሳስቶ ሕገወጥ ከሚሆን ጥቂቶች ቢሰቃዩ ይመረጣል» በሚል መንፈስ ነው የሚፈጸመው። ከአንድ ሺ ስምንት መቶ አመታት በፊትም የእስራኤል ሕዝብ ባለስልጣናት በክርስቶስ ላይ ተመሳሳይ ምክንያት ሰጥተው ነበር። ቀያፉ እንዲህ ነበር ያለው «ሕዝቡ ሁሉ ከሚጠፋ ስለ ሕዝቡ አንድ ሰው ቢሞት የሚሻል መሆኑን አታስተውሉም?» (ዮሐ 11፥50) ። ይህ አስተሳሰብ እንደ አንድ ወሳኝ አስተሳሰብ ሆኖ ይቆጠራል። በመጨረሻም አራተኛይቱን ትእዛዝ ሰንበትን ቀድሰው የሚጠብቁ ሰዎች ብርቱ ቅጣት እንደሚገባቸው፣ እነርሱን የሚያወግዝና ከተወሰነ ጊዜ በኋላም ለሞት እንዲዳርጓቸው ለሕዝቡ ነጻነትን የሚሰጥ ድንጋጌ ይወጣል። በጥንቷ አለም የነበረው ካቶሊካዊነትና በአዲሱ አለም ያለው ከሀዲ ፕሮቴስታንትነት የመለኮትን ሕግ (ትእዛዛት) በሚያከብሩት ላይ ተመሳሳይ እርምጃ ይወስዳሉ። በዚያም ጊዜ የእግዚአብሔር ሕዝቦች (ወገኖች) ነብዩ ኤርምያስ «የያእቆብ የመከራና የስቃይ ዘመን» ብሎ ወደተነበየው ጊዜ ይገባሉ። (ኤርምያስ 30፥5-7)። ◆ **ኤለን ጂ. ኋይት**

*ተከታዩ በሚቀጥለው እትም ይቀጥላል*

## *ለዚያኛው ቀን* *(ከገጽ 1 የዞረ)*

ከዚያም የንግሥና ዘመኑ ሲያበቃ ወደ ምድረበዳዋ ደሴት ሳይሆን በጣም ወደለማችውና ውብ ወደሆነችው ደሴት ሄደ ይባላል ።

ይህ ታሪክ ከፊታችን ለሚጠብቀን ፍርድ ዛሬ በመዘጋጀት እንድንኖር ያስተምረናል። ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ «መልካም ወይም ክፉ እንዳደረገ እያንዳንዱ በሥጋው የሠራውን ብድራት ይቀበል ዘንድ ሁላችን በክርስቶስ በፍርድ ወንበር ፊት ልንገለጥ ይገባናልና» (2ኛ ቆሮ 5፥10)። በዚያን ጊዜ ሰብአዊው ፍጡር ለሁለት ይከፈላል፥ 1ኛ) የዘላለሙን መንግሥት የሚወርሱና 2ኛ) «...ከጌታ ፊትና ከኃያል ክብሩ ተለይተው በዘላለም ጥፋት የሚቀጡት» ናቸው። (ማቴ 25፥31-46 ፣ 2ኛ ተሰሎ1፥7-9)

የዘላለሙን መንግሥት የሚወርሱት ይህን መንግሥት ለመውረስ ራሳቸውን ያዘጋጁ ናቸው። ራሳቸንን ለማዘጋጀት መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ሲል

**(በገጽ 8 ይቀጥላል)**



# መንግሥተ ሰማያት ለብርቱዎች

ወይዘሮ ውዴ ካሰኝ በሹፌርነት ለረጅም አመታት ሲያገለግሉ ከነበሩት ከባለቤታቸው ከአቶ ወልደጻድቅ ዳኜ ጋር ቀበና በቤተክርስቲያናችን ግቢ ውስጥ ይኖሩ ነበር። አንድ ቀን ሲስተር አበባ ገብረሚካኤል የምትባል ክርስቲያን ወ/ሮ ውዴን ከባድ ጥያቄ ጠየቀቻቸው። «እስከዛሬ ወንጌልን ይሰማሉ፤ለምንድነ ነው የማያምኑትና የማይጠመቁት?»።

ወ/ሮ ውዴ ማታ ሳይተኙ በፊት ተንበርክከው «እኔ መኃይም ነኝ፣ምንም አላውቅ፣መንገዱን አንተ አሳይኝ» ብለው ወደ አምላክ ጸለዩ። ሌሊቱን በዚያው ሌሊት ሕልም አለሙ። አንዴ የቤተክርስቲያናችን ፓስተር ሰዎችን ወደ መንግሥተ ሰማያት ሲመራ እሳቸውም ሲከተሉት አዩ። ሕልሙን ባለሙ በጠዋቱ ወ/ሮ ውዴ ከፓ/ር ብርሃኑ ጋር የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጀመሩ።

የነፍስ አባታቸውን፣ወዳጅና ዘመድን ሳይፈሩ ካመኑ በኋላ ተጠመቁ። በሚጠመቁበትም ጊዜ ብቻቸውን ለመጠመቅ አልፈለጉም ነበርና፤ጎረቤታቸው አብራ ተምራ፣ አምና አብራ ተጠመቀች። እኚህ የተወደዱ እናታቸን ወሮ ውዴ በጌታ ማረፋቸውን ሰሰማ ሕሊናዬ የሚከተሉትን እንድጽፍ ገፋፋኝ፥



እማማ ውዴ ጎረቤት ጓዴ  
እናት እህቴ ዘመዴ  
ግራ ገብቷቸው  
ቀኑ ጨለማ ሆኖባቸው  
የመዳን ዘዴው ጠፍቶባቸው  
አጥብቀው ለመኑት ጌታን  
እንዲጠቁማቸው መንገዱን  
በናፍቆት በጉጉት  
አቤቱ አቤቱ በማለት  
ወተወቱት ለመኑት።  
ተኝተው በህልም ማታ  
አነጋገራቸው የኛ ጌታ  
ሰጣቸው መመሪያውን  
አሳያቸው መንገዱን  
ክርስቶስ ጌታ መሆኑን አወቁ  
ተማሩ አመኑ ተጠመቁ  
በመንፈስ ተጎበኙ  
ሰላም ደስታን አገኙ  
በቀራንዮ ደም  
ታተሙ ለዘላለም  
እጣ ፈንታቸው ተወሰነ  
በጻድቃን በኩል ሆነ  
ለቀሳውስት ሳይበገሩ  
ለራሳቸው ሳይራሩ  
የሰው ፊትንም ሳይፈሩ  
ከብርቱዎች ጋር ተቆጠሩ።

«ከመጥምቁ ዮሐንስ ዘመን ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ መንግሥተ ሰማያት በብዙ ትገፋለች የሚያገኟትም ብርቱዎች ናቸው» (ማቴ 11፣12) ◆

*ግርማ ዳምጤ ከአሜሪካ*

**የትንቢት ቃል**  
**ዌብ ሳይትን ይጎብኙ!**  
**www.yetnbitkal.de**

## የሃይማኖቱ አለም ወቅታዊ ዜናዎች

የ58ኛው ጀነራል ኮንፈረንስ አጠቃላይ ስብሰባ አጭር ሪፖርት

«ትራንስፎርምድ ኢን ክራይስት (በክርስቶስ የተለወጠ ሕይወት)» በሚል ርእስ ከሰኔ 29 እስከ ሐምሌ 9 2005 ድረስ በሴይንት ሉዊስ ሚዙሪ በተካሄደው የጀነራል ኮንፈረንስ አለም አቀፍ ስብሰባ እስከ 40000 ሰዎች ተካፍለውበት ነበር። በኤድዋርድ ጆንስ ዶም ውስጥ በሚገኘው አሜሪካ ሴንተር በተባለው ትልቅ አዳራሽ ውስጥ ደግሞ 560 የአድቬንቲስት ድርጅቶችና ተቋሞች (ትምህርት ቤቶች፣ማተሚያ ቤቶች፣የህክምና ተቋሞች፣የቴሌቢዥን ጣቢያዎች፣የተለያዩ የማሕበራዊ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች እንዲሁም በዛ ያሉ ሌሎች የአድቬንቲስት ድርጅቶችና ተቋሞች) በተለያዩ አገሮች የሚሰጡትን አገልግሎቶች አስተዋውቀዋል።

ከዚያም ባሻገር በየጠዋቱ እና በየምሽቱ እንዲሁም በ2 ሰንበቶች መንፈሳዊ መልእክቶችና ልዩ የመዝሙር፣የሙዚቃና የድራማ ዝግጅቶች ተካሂደዋል። በእነዚህ በአለም አቀፍ አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን የሚካሄዱት አገልግሎቶች በተሰራጩባቸው ቀናቶች 230 ፈቃደኛ ወንድምና እህቶች ወደ 20 የተለያዩ ቋንቋዎች ከተለያዩ አገር ለተገኙት እንግዶች ተርጉመዋል።

በ204 አገሮች ውስጥ የሚገኙትን 14,3 ሚሊዮን አድቬንቲስቶች ወክለው የመጡት 2000 መልእክተኞች ባደረጉት ስብሰባ ያለፉትን አምስት አመታት የሥራ ሪፖርት ካቀረቡ በኋላ አዲስ የአገልጋዮች ምርጫን በማድረግ የአምስት አመት የሥራ እቅድ አውጥተዋል። በተጨማሪም በቤተክርስቲያን መመሪያ ጉዳዮችና በአድቬንቲስት ቤ/ክ መሰረታዊ እምነቶቸ ላይ ውይይት በማድረግ አንድ አዲስ የእምነት መሠረት እንዲጨመር ወስነዋል።

ሌላው ደግሞ የዶክተር ኤላ ሉዊስ ስሚዝ ሲሞንስ እንደምክትል ፕሬዚደንትነት ሆኖ መመረጥ የዚህን አመት አለም አቀፍ ስብሰባ ልዩ እንዲሆን አድርጎታል። ከዘጠኙ ምክትል ፕሬዚደንቶቸ አንዷ በመሆን ለመመረጥ ዶክተር ኤላ በአድቬንቲስት ቤ/ክ ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያዋ ሴት አገልጋይ ለመሆን በቅተዋል። ወንድም ጃን ፓውልሰን ለሚቀጥሉት አምስት የአገልግሎት አመታት እንደገና በፕሬዚደንትነት ተመርጠዋል።

«ኢምፓክት ሴይንት ሉዊስ» በሚል ልዩ አገልግሎት ላይ ከ 15 አገሮች የመጡ 400 ወጣት አድቬንቲስቶች የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም በሴይንት ሉዊስ ከተማ ለሚገኙት ሰዎች ወንጌልን አሰራጭተዋል (የመንገድ ተዳዳሪዎችን በመመገብ፣ስእሎችን በመሳል፣በመዝሙር አገልግሎት፣ልዩ የህጻናት ዝግጅቶች በማቅረብ፣የጽዳት አገልግሎት በመስጠት)።

58ኛው የጀነራል ኮንፈረንስ ስብሰባ ሰንበት ሐምሌ 9 የአድቬንቲስት ቤ/ክ ከሚገኙባቸው 204 አገሮች የመጡ ወንድሞች፣እህቶች እንዲሁም ህጻናቶች አገራቸውን በመወከል ባንዲራቸውን እያውለበለቡ አንድ በአንድ በሰልፍ በሄዱበት «ፓራድ ኦፍ ኔሽንስ» ተብሎ በተሰየመው ትእይንት ተጠናቀቀ።

«ጌታ ተመልሶ ከመጣ በሰማይ፣ካልመጣም ደግሞ ለ59ኛው ጀነራል ኮነፈረንስ ስብሰባ በአትላንታ አሜሪካ እንገናኝ» በማለት ወንድምና እህቶች ሰላምታ ተሰጣጥተው ተለያይተዋል።

በርከት ባሉ ፎቶዎች የተደገፈውን ሰፊ ሪፖርት ማንበብ ከፈለኩ ይህንን ዌብ ሳይት ይመለከቱ፥-

www.yetnbitkal.de/html/news.html ◆

በኢትዮጵያ አድቬንቲስት ዩኒየን አዲስ መሪዎች ተመርጠዋል። ፓ/ር አለሙ ሃይሌ ፕሬዚደንት ሲሆን ወንድም ቢቂላ መርጋ ደግሞ ጸሐፊ ነው። ለሁለቱም ደስታችንንና መልካም ምኞታችንን እንገልጻለን።  
(ምንጭ፥ ሰላምታ ኒውስሌተር) ◆

# የትንቢት ቃል

Yetnbit Kal
P.O.Box 1749
90006 Nuernberg
Germany

Editors:
Dawit Mehari
Dawit Mengistu

Tel & Fax 0049 - 911- 41 57 89
Tel & Fax 0049 - 89 - 22 24 48
E-Mail: yetnbitkal@yahoo.com
Web: www.yetnbitkal.de

ይህንን የጽሑፍ አገልግሎት በገንዘብ ለመደገፍ የምታስቡ ሁሉ በዚህ የባንክ ቁጥር መጠቀም ትችላላችሁ። ለድጋፋችሁ በቅድሚያ ከልብ እናመሰግናለን እግዚአብሔር ይባርካችሁ!

**IBAN:**
DE32 7605 0101 0002 0599 32
**SWIFT-BIC:**
SSKNDE77

ይህች «የትንቢት ቃል» የምትለው የአድቬንቲስት መጽሔት በጀርመን አገር ተዘጋጅታ በአመት ሶስት ጊዜ ትወጣለች። አላማዋም በአገራችንና በተለያዩ አህጉራት የሚገኙትን ወገኖቻችንን ለየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ለማዘጋጀት ነው። ምንም ዋጋ የማይከፈልባት በነጻ የምትላክ እንደሆነች ልንገልጽልዎ እንወዳለን። ስለዚህ ለእርስዎም ሆነ ለሌሎች ጽሑፉ እንዲደርሳቸው ለሚፈልጉት ሰዎች አድራሻዎችን ቢያሳውቁን መጽሔቱን እንልካለን።

በዚህች መጽሔት መልእክት ተባርከው እንደሆነና አስተያየትም ሆነ ጥያቄ ካለዎ ሃሳብዎን ቢገልጹልን በጣም ደስ ይለናል።

## አዲስ መጽሐፍ




ፓስተር ጥሩነህ ወ/ሥላሴ እጅግ ብዙ የተለፋበትንና የታሪክ አፍቃሪዎች ሁሉ የሚወዱትን "Adventism in Ethiopia"የሚል መጽሐፍ በእንግሊዘኛ ጽፈው አቅርበዋል። ለበለጠ ኢንፎርሜሽን ይህንን ዌብሳይት ይመልከቱ
**www.ethiopiaadventist.com**

## አዲስ መጽሐፍ




አዲስ እጅግ ጠቃሚ የሆነ የጤና መጽሐፍ በኢትዮጵያ አድቬንቲስት ማተሚያ ቤት ታትሞ ለሽያጭ ቀርቦአል። ለበለጠ መረጃ በአ.አ. የአድቬንቲስት መጽሐፍት መደብር ይጠይቁ።

## የጥያቄዎ መልስ

**በ58ኛው ጀነራል ኮንፈረንስ ስብሰባ ላይ የተጨመረው አዲስ የአድቬንቲስት ቤ/ክ መሠረታዊ እምነት ምን ይላል?** *ሰ.መ. ከጀርመን*

በ204 አገሮች ውስጥ የሚገኙትን 14,3 ሚሊዮን አድቬንቲስቶች ወክለው በሰሜን አሜሪካ በሴንት ሉዊስ ከተማ በተካሄደው 58ኛው የአድቬንቲስት ቤ/ክ አለም አቀፍ ስብሰባ ላይ የተገኙት 2000 መልእክተኞች በ27ቱ የአድቬንቲስት ቤ/ክ መሠረታዊ እምነቶቸ ላይ አንድ ሌላ መሠረታዊ እምነት እንዲጨመር ወስነዋል። ይህም «ግሮዊንግ ኢን ክራይስት» (በክርስቶስ ማደግ) የሚለው ሲሆን፤ በዝርዝሩ እንደሚከተለው ይነበባል፥-

«በመስቀል ሞቱ አማካኝነት የሱስ በርኩሳን መናፍስት ላይ ድል ነሳ። በምድራዊ አገልግሎቱ ጊዜ እርኩሳን መናፍስት ለየሱስ ታዘዙለት፣እሱም ሃይላቸውን ሁሉ በመሰባበር አንድ ጊዜ (በፍርድ ጊዜ) ለዘላለም እንደሚጠፉ አረጋገጠ። የሱስ በርኩሳን መናፍስት ላይ ድል ስለነሳ እኛም ከየሱስ ጋር በሰላም፣በደስታ እና በፍቅሩ ሕይወታችንን እስከመራን ድረስ በእኛ ላይ ሊሰለጥኑ በሚፈልጉት ክፉ መናፍስት ላይ ድል ነስተናል። አዳኛችንና ጌታችን ከሆነው ከየሱስ ጋር የማያቋርጥ ግንኙነት ስላለን፤ቀድሞ ስንለማመዳቸው ከነበሩት መጥፎ ልምዶች ነጻ ወጥተናል። ከእንግዲህ ወዲህ በጨለማ፣በፍርሃት፣ባለማወቅ እና እንደቀድሞው ትርጉም የለሽ ሕይወት አንመላለስም።

**በክርስቶስ ማደግ**

በየሱስ ባገኘነው አዲስ የነጻነት ሕይወት፥ የርሱን ባሕርይ ወደመምሰል ለማደግ፣በየቀኑ በጸሎት ከእርሱ ጋር ህብረትን ለማድረግ፣በየቀኑ ከቃሉ በሚገኘው ኃይል ለመኖር፣በየቀኑ ቃሉን ለማንበብና ቃል ኪዳኖቹን ሁልጊዜ ለማስታወስ፣የምስጋና ውዳሴን ለማቅረብ፣ከወንድሞችና እህቶች ጋር ለስግደት ለመሰብሰብ እንዲሁም በወንጌል ስርጭት አገልግሎት ለመተባበር ተጠርተናል።

ራስን ሙሉ በሙሉ በሰጠ አገልግሎት በአካባቢያችን ያሉትን ነፍሳት ስናገለግልና የደህንነትን መንገድ ስናሳይ እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ከእኛ ጋር ስለሚሆን፤እርሱ እያንዳንዱ አገልግሎታችንን ልዩ መንፈሳዊ ልምምድ እንዲሆንልን ያደርገዋል። »

(መዝ 1፥1-2፣መዝ 23፥4፣መዝ77፥11-12፣ቆሎ 2፥6,14,15፣ሉቃስ 10፥17-20፣ኤፌ 5፥19-20፣ኤፌ 6፥12-18፣1ኛ ተሰሎ 5፥23፣2ኛ ጴጥ 2፥9፣2ኛ ጴጥ2፥18፣2ኛ ቆሮን 3፥17-18 ፊሊ. 3፥7-14፣1ኛ ተሰሎ 5፥16-18፣ማቴ 20፥25-28፣ዮሐ 20፥21፣ገላ5፥22-25፣ሮሜ 8፥38-39፣1ኛ ዮሐ 4፥4፣ እብራ 10፥25) ◆

## *ለዚያኛው ቀን..(ከገጽ 6 የዞረ)*

ያስተምረናል፥- የሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ማመን ይኖርብናል (የሐዋ ሥራ 16፥31)፣ ኃጢአታችንን መናዘዝ (የሠዋ ሥራ 17፥30,31)፣ ለኃጢአት ይቅርታ መጠመቅ (በጥልቀት ጥምቀት) (የሐዋ ሥራ 2፥38) እና በሰዎች መካከል ስለክርስቶስ መመስከር (ሮሜ 10፥9,10)። በሕይወት ዘመናችን እግዚአብሔርን እየተከተልን ከኖርን ራሳችንን በማዘጋጀት እንኖራለን ማለት ነው።(1ኛዮሐ 1፥7)

ማርቲን ሉተር «በሕይወቴ ሁለት ወሳኝ ቀናቶች አሉኝ፤ እነርሱም ዛሬ እና "ያ ቀን" ክርስቶስን ለፍርድ የምገናኝበት ቀን ነው።» ሲል ይደመጥ ነበር ይባላል። እኛም ዛሬን "በዚያ ቀን" ብርሃን እንኑረው።

እርስዎስ ለዚያኛው ቀን ተዘጋጅተዋልን?◆

***ዴቢድ ኤ. ሳርጀንት, ከእንተርኔት የተገኘ***

**(ትርጉም ሰለሞን ቁሜ)**